የምጽአቱ የምሥራች

ቅጽ 81 (ቁጥር) 4 (964 ቅጽ 80 ቁጥር 7/8 955 - 956)

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጽኑ አስፈላጊነት እና የፍቅር ልዩ ከፍታ

(በስብከት ንጉስ ቻርለስ ስፐርጂን እና በሣሙኤል ቻድዊክ)

ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተመሠረተች ተቋም ስትሆን ሠማያዊና ምድራዊ ኃላፊነትና ስልጣን ያላት ናት።

ቤተክርስቲያን በተለያየ ስያሜዎች ብትጠራም ዋና መሠረቷ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ በአማኞች ህብረት የምትገለጥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ እግዚአብሔር የሚጠቀምባት ናት። ማቴ 28፡19 16፡18 1ቆሮ 3፡11 12፡3

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ደቀ መዛሙርቱን እንዲጠባበቁ የሰጠው ተስፋ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲወርድባቸው ነበር። ሐ.ሥራ 1፡4

የመንፈስ ቅዱስ መላት በኃይል በተከታዮቹ በአማኞቹ ላይ መፍሰስ በበዓለ ሃምሳው በጰንጠቆስጤ ወይም ጸራቅሊጦስ እለት በጽኑ የሚፈለገውን ያህል ዛሬም በጽኑ ይፈለጋል። በተለይም የፈውስ የፍቅር የቅድስናና የሰላም ምሳሌ የሆነው የአማኞች ሕብረት (ቤተክርስቲየን) በዚህ ዘመን ባለበት ከፍተኛ ጉድለት የመንፈስ ቅዱስ አስፈላጊነት እርግጥ እጅግ ተፈላጊ ነው።

የቤተክርስትያን አካላት ሕይወት

የጌታ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ጌታ ከማረጉ በፊት የሰጠውን የተስፋ ቃል ማስፈጸምና በአማኞች ሕይወት መግለጥ ነው። "ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ"(ሐዋርያት ሥራ 1፡2)። ጌታ መንፈስ ቅዱስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጀመረውን አገልግሎት በንቃት የሚያስቀጥል ነው። መንፈስ ቅዱስ የማዳን የመቀደስ የማንጻት እንቅስቃሴዎችን በአማኞች ሕይወት፣ አንደበትና ኑሮ ይገልጻል።

የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትና ሥራ ወይም ጸጋዎች በማንም ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ ፓስተር፣ ቄስ፣ ዲያቆን ወዘተ በውክልና የሚሰጥ የሚተላለፍ ሳይሆን አማኞች በግል በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር የሚያገኙት ስጦታ ነው። "በሰማይ ያለው አባት ለሚለምነት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸው።" (ሉቃስ 11፡13)

በሰዎች ጥበብና እውቀት የሚመራ የቤተክርስቲያን ማንኛውም ፕሮግራም ለውድቀት የሚዳረግ ሲሆን በቅዱስ መንፈስ የሚመራ አገልግሎት ግን

ማንኛውንም ጥቃትና መሰናክል የሚያልፍ ነው።

በቤተክርስቲያን ታሪክና በአማኞቹ ሕይወት መከራ፣ስደት፣ ውጊያ የሚታይ ሲሆን ይህንን ሁሉ ግን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እያሸነፈ፣ እያከሸፈ፣ እያሳለፈ፣ ክርስቲያኖችን ለዛሬው ዘመን አድርሷል። በዘመናችንም በመከራ የሚያልፉም ሆነ በምቾትና በአለማዊ ሥራዎች ሳይበገሩ ክርስቶስን በመመስከር የሚተጉ የእግዚአብሔር ጥቂት ልጆች በመላው ዓለም ይገኛሉ።

"ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል" (ሮሜ 8:35)

የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች በሥርዓት መካሄድን ቅዱስ ቃሉ የሚደግፍ ቢሆንም እነዚህ ሥርዓቶችን በልማድ ባለመረዳት ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውጭ ማከናወን ግን መዛልና ውድቀትን ስለሚያስከትል አማኞች ሁሉ የቤተክርስቲያንን ሥራዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት በመቀጣጠል ሊንቀሳቀሱ ይገባል(ኤፌሶን 5:18፣ ሐዋርያት 6:3)።

በመንፈስ መሉት መመላለስ በእግዚአብሔር ቃል በሥርዓት መኖር እንጂ ከቅድስና ውጭ በስሜት መኖር አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ ስራና ኃይል ምንጭ

የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ስጦታዎች ከእግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስራዎች ውጭ አይደሉም። የተፈጥሮ ሰብአዊ ነገር በሰው ሥራ የሚገለጥ ሲሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ስራ ግን የመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ኃይል ነው። "የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፣ በመንፈስ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም" (ዘካርያስ 4:6)።

ከጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ ከቅዱስ መጽሐፍ እንደምናነበው የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴም ሆነ ጅማሬ በመንፈስ ቅዱ ምሪትና ኃይል ነው። ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎችና ስጦታዎች ሁሉ ምንጩ እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉና ቅዱስ መንፈሱ ነው።

አጋንንት በአማኞች የሚታዘዙትና ሰዎችን ለቅቀው የሚወጡት የታመመ ፈውስ የሚያገኙበትና ከመነሻውም ሰዎች ኃጢያተኛ መሆናቸውን ተረድተው ወደ ጌታ የሚመለሱት የበጎ ገነሮች ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ጀማሪነት ነው። (የሐዋርያት ሥራ 1:8፣ ዮሐንስ ወንጌል 16:8)

በመጨረሻው ዘመን ለሕይወትና ለአገልግሎት የመለኮታዊ ኃይልን ስለማሰብ

(በሪቸ ካርማይክል፣ የምጽአቱ የምስራች አሳታሚ)

በዚህ በአሜሪካ የምጽአቱ የምስራች አገልግሎት ቢሮዎች የመጨረሻው ቀን ምልክቶችን እንንደምንረዳው አንባቢዎቻችንም በያሉበት ይረዱታል ብለን እናስባለን።

ስለመጨረሻው ዘመን ጉዳዮች የክርስትና እምነት ጀማሬና ፈጻሚ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቃላት መነሻ ዋቢ መረጃዎቻችን ናቸው። የመንግስታት በመንግስታት ላይ መነሳት፣ ረሀብ፣ የምድር መናወጥ፣ ቸነፈር፣ በልዩ ልዩ ስፍራዎች በዓለማችን ላይ መታየት ምልክቶቹ ናቸው(ማቴዎስ 24:6)።

ዓለምን በብዙ እጥፍ ሊያወድሙ የሚችሉት የጦር መሳሪያዎች በአያሌ መንግስታት ርህራሄ በሌላቸው ጭምር መያዙን እናውቃለን።

በዓለም ዙሪያ ቀድሞ ከነበረው ክፋት የባሰ ክፋት ረሀብ ችነፈር መፈናቀል ጥላቻ ማየታችን የመጨረሻው መጨረሻ መቅረቡን ያረጋግጥልናል። ግሎባላይዜሽን በተባለው ክስተት ብዙ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች የዚህ ቅዱስ ወንጌል መስፋፋት ጭምር የሚካሄድ ቢሆንም በግሎባላይዜሽን ሽፋን በመላው ዓለም የሚስፋፋውን የጥፋት ልጅ የሐሰተኛው ክርስቶስን ስራዎች ከነምልክቶቹ በማየት ልንዘጋጅ ልንጠብቅ፣ ልንጠነቀቅና ሌሎችን ልናስጠነቅቅ ይገባል(ማቴዎስ 24፣ ቆላስያስ 1:29)

ተጨማሪ የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ደቀመዛሙርቱ የጥንት ቤተክርስቲያን አባቶችም እንዳስተማሩት ከቅዱስ ቃሉ የሚጣረሱ ድርጊቶችና ልማዶች ቤተክርስቲያን ተብለው ራሳቸውን በሚጠሩት ሳይቀር በመታየት ላይ ነው (ማቴ 24:9)።

ሐዋርያው ጳውሎስም በጌታ መንፈስ በመመራት የመጨረሻው ዘመን ክፋቶችን ለእምነት ልጁ ለጢሞቴዎ በጻፈለት ቅዱስ ቃሉ ያስተምረናል(2 ጢሞቴዎስ 1:7)

በልዩ ልዩ ሁኔታ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በችግርና በህመም ውስጥ ቢያልፉም የመጨረሻውን ዘመን ፈተናና መከራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲወጡ በብርቱ መጸለይና መጋደል ይኖርባቸዋል(2 ቆሮንቶስ 12:9፣ 1 ተሰሎንቄ 1:5)።

የጎደለ መንፈሳዊነት ይታደሳል

(በዌስሌ ዱዌል)

መንፈስ ቅዱስን በቅዱስ ቃሉ መሰረት ስንሞላ ለእግዚአብሔር ፍጹም መገዛትን መታዘዝን ለቤተክርስቲያን፣ ለማህበረሰብ፣ ለሀገርና ለመላው ዓለም በረከት እንሆናለን።

ቅዱስ መንፈስ በአማኞች ሕይወት ሲፈስና ሲሰራ ፈተናዎች ምን ያህል ቢበዙ የሰይጣን ሥራዎች ምን ያህል ቢበረክቱ አማኞች ችግሮችን በአሸናፊነት ይወጣሉ(1 ጢሞቴዎስ 5:22፣ 1 ዮሐንስ 3:3)።

ሆኖም ግን መንፈሳዊ ኃይል ሁል ጊዜ አብሮን የማይቆይበት ሁኔታዎች በልዩ ልዩ ፈተናዎችና በራሳችን ያለመታዘዝ ከእኛ የሚርቅባቸው ጊዜያት አሉ። እነዚህ ወቅቶችን ማለፍና በጌታ መጽናት የምንችለው አሁንም በጌታ በመታመን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚሰጠንን የንስሃና የጥሞና ኃላፊነቶችን በመወጣት ነው (ዘካርያስ 4:1፣ 1ተሰሎንቄ 5:21)

የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በሕይወታቸውን የሚቀጥሉት በጌታ ቤት ሥራ በተጋን ቁጥር ይሆናል።

የምንኖረው በዓለም እንጂ በዓለማዊነት ሥርዓት አይደለም። ስለዚህ በምንኖርበት ክፉ ዓለም በማስተዋል ከዓለም ተለይተን መኖር ይገባናል (ዮሐንስ 17:15)።

ከሌሎች ወንድሞችና እኅቶች ጋር ህብረታችን በተጠናከረ ቁጥር የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሥራዎች በሕይወታችን ይበዛሉ (2 ጴጥሮስ 2:7፣ ዘካሪያስ 2:8)

ለጌታ ያለመታዘዝ የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና ሥራዎች ይቀንሳል። በሌሎች ላይ የፍርድ ቃል ማብዛት መንፈስ ቅዱሱን ያሳዝናል፤ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ይጎዳል(ሮሜ 14:4፣ ኤፌሶን 4:30)።

ራስ ወዳድነት መንፈሳዊ ሕይወትን ከሚጎዱት ነገሮች ሁሉ የከፋው ነው። ራስን መውደድ ለራሳችን ተገቢውን መንፈሳዊና ስጋዊ ክብካቤ የሚከለክል ሳይሆን የሌሎችን ጉዳትና ውድቀት ሳይገደን ለግል ሕይወታችን ብቻ በስግብግብነት የምናደርገው ሩጫና ክፉ ውድድር ነው። በዘመናችን ያለች ቤተክርስቲያን በክርስቶስ እውቀት በማደግ ሰዎችን በበረከት ከመሙላት ይልቅ ከሌሎች ወገኖች ጋር ፉክክር በማድረግ ሁሉንም ለግል ጥቅምና ዝና ለማዋል በሚደረግ ሩጫ በጥፋት ላይ ትገኛለች(2 ጢሞቴዎስ 3:2)

ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን አማኝና መላዋ ቤተክርስቲያን ከትዕቢትና ከዓለማዊ ምኞት በመራቅ የጎደለ መንፈሳዊነትን በንስሃ ለመመለስ እንዘጋጅ (ሉቃስ 10:20፣ 2 ቆሮንቶስ 4:7)።

የእግዚአብሔርን ኃይል በብርቱ ፈልጉ

(በጀምስ ስሚዝ)

በዚህ ዘመን መንፈሳዊ ኃይል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እንደሚያስፈልገን የማይረዳ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ የሚል እራሱን ይመርምር። የሰዎች የሸንገላ ቃላት ለእኛ ለአማኞች ጥፋት እንጂ ስኬትን አያመጡልንም። በክርስቶስ በማመን ምኞት ድሎትና ብልጽግና ይገኛል የሚለው አሳች ትምህርት መጨረሻው ከክርስቶስ እውነተኛ መንገድ ጨርሶ የሚያስወጣ ሐሰተኛ ትምህርት ነው።

እራሳችንን በመካድ የክርስቶስን መስቀል በመሸከም በእምነት መኖር ከመቼውም ጊዜ በላይ የሚያስፈልገን ነገር ነው። ያለ ጌታ ክርስቶስ አንዳች በጎ ነገር መሥራት እንደማንችል አማኞች ልናውቅ ይገባል(ሉቃስ 9:20፣ ሜቴዎስ 5:30)።

ጌታ በቃሉ የሚያስተምረን ራሳችንን የምንክደው ማንነታችን በመካድ ወይም የሰውነት አካላችን ቢያሰናክለን ቆርጠን ማስወገድ ሳይሆን ለዓለም ለሰይጣንና ለስጋ የሚዳርገንን ክፉ ልማድና ድርጊቶች በማራቅ ራሳችንን የሕይወታችን መሪና ፈጻሚ አድርገን ማመንን በመጣል በጌታ ላይ እምነታችንን፣ ሕይወታችንን አካላችንን፣ ቤተሰባችንን፣ ሀገርና ማኅበረሰባችንን መስጠት መሆኑን ለማስተማር ነው።

እራሳችንን በግል በመፈተሽ በመመርመር በንስኃ በመስተካከል በፍጹም ኃይልና ልብ በጌታ በመታመን መመላለስ ይኖርብናል(ሐዋርያት 1:8)።

የበጉ የክርስቶስ ደም ኃይል

(በሮይ ሄሰን)

ለሚጠብቀን መንፈሳዊ መነቃቃት ተገዳዳሪ የሆነው ጉዳይ በመንገዳችን ላይ ነው። ይህን ተግዳሮት ምንም ሳይሆን ኃጢያት ብቻ ነው።

ይህንን ተግዳሮት የሚያስወግድ አንድ ብቸኛ መንገድ ወይም መፍትሔ ደግሞ በበጉ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የሚገኘው የመቀደስ፣ የመንጻትና ኃይል የመቀበል ድርጊት ስኬቶች የተትረፈረፉ ናቸው። በበጉ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም

በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ሰላም ይፈጠራል (ቆላሲያስ 1፡20)። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በሰይጣን አሳሳችነት የተጣላውን የሚያስታርቅ ለሰው ዘር የተሰጠውን በረከትና የዘላለም ሕይወት የሚያጎናጽፍ በክርስቶስ ደም የሚገኘው ኃይል ብቻ ነው። በክርስቶስ ደም በሚገኝ ኃይል ኃጢያት ሁሉ ይታጠባል(ቆላሲያስ 1፡14፣ ዮሐንስ 6፡54፣ ራዕይ 12፡11)

በክርስቶስ ደም የማያቋርጥ መንጻት ይገኛል(1 ዮሐንስ 1፡7)። በክርስቶስ ደምና ኃይል ሰዎች ከማንኛውም እስራት ነጻ ይሆናሉ(ወደ ዕብራውያን 9፡14)። ትልቁ ጥያቄ ይህ እንዴት ይከናወናል? ምንስ ማለት ነው? የሚለው ነው።

የደሙ ኃይል ምንድነው?

የክርስቶስ የደሙ ኃይል ምንነት የሚጀምረው የእስራኤል ልጆች ከአስጨናቂው የፈርኦን ባርነት ነፃ የወጡበት በበሩ መቃን ላይ የተረጨው ደም የሚነሳ ነው። ኦሪ ዘፀ 12

ይህ የክርስቶስ ደም ኃይል የጌታችን የወንጌል መልዕክቶች ውስጥ የተገለፀ ሲሆን በዮሐንስ ራዕይ በበለጠ ተብራርቶ ይገኛል። ራዕ 7፡14

በጉ የሚለውን ቃል ለሰው ዘር ኃጢያት የተሰዋው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል። ዮሐ 1፡29

የበጉ ሚስጥር ከመስዋዕትነቱም በላይ የትህትናና የቅንነት መለያ ሆኖ በቅዱሳት መፃህፍት ቀርቧል። ማቴ 11፡29 ዮሐ 6፡38

የመታዘዝ ምልክትም ነው። ፊሊ. 2፡8 ጌታችን ኢየሱሱ ክርስቶስ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም ሲመቱትም መልሶ አልመታም። ይህ ምን አይነት ልዩ ባህሪይ ነው?

ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው የሆነው ክርስቶስ በሰውነቱ ከዚህ የተነሳ ከሌላው ሰው በፍጹም የተለየ ነው። በቀራኒዮ መስቀል ላይ ህይወቱን ለሰው ዘር ሁሉ ሲሰጥ በትህትና ራሱን ዝቅ በማድረግ ነበር። " እንደበግ በሸላቾቹ ፊት ተመላለሰ አፋንም አልከፈተም" (ኢሳ 53፡7)

ሲሰድቡት ሲያንገጥጡበት በጥፊ ሲመቱት ደሙም ከጎኑ ሲወጣ የታየው ሁኔታ እንደ በግ መታረዱን የሚያሳይ ነው።

በመስቀል ላይ ክርስቶስ የታረደልን የእግዚአብሔር በግ በመሆን ነው። በብሉይ ኪዳን ሥርዓት በኃጢያት ሥርየት ብዙ እንስሳት የሚሰውትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመስቀል ተሰዋልን። ዕብ 9፡14

የመጀመሪያው ሰው አዳም በኃጢያት ምክንያት ለሰው ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን ቁጣ ቢያመጣም ሁለተኛው ሰዉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ኃጢያት ለማስወገድ የሰውን ዘር ሁሉ በደሙ ነፃ አወጣ 2ቆሮ 5፡17 ዘፍ 2፡7

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በረከት የተጠበቀልንና ኃጢያታችን ሁሉ የተሰረየልን በበጉ በክርስቶስ ደም በተገኘልን መስዋዕትነት ነው 1ቆሮ 2፡16 ፊል 2፡5

የበጉን ኃይል ለመቀበል ዝግጁ ነን?

ይህንን በበጉ በክርስቶስ የተሰጠንን የመዳን የመንፃት የመባረክ እድል የሚከለክል ራስ ወዳድነትና

ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዘ ብቻ ነው።

በተሰበረ ልብ ቅዱስ ቃሉን ሰምተን እስከታዘዝን ድረስ የበጉ ደም ኃይል ለእኛ የተለቀቀ ይሆናል። ማቴ 5:23

የበጉ ደም ኃይልን ዘወትር ለመቀበል በእውነተኛ ንሰሐ እንዘጋጅ።

የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን፣ሕይወትና ኃይል አለው

የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ለማወቅ መጽሐፍን በከፈትን ቁጥር በእግዚአብሔር ፍርሃት እና አክብሮት ሊሆን ይገባል። ከእግዚአብሔር ቋንቋ የበለጠ ምን ድንቅ ነገር ሊኖር ይችላል?

የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ድምጹን መስማት ብቻ ሳይሆን በመሉ ልብና ስሜት እግዚአብሔርን ማዳመጥን ይጨምራል።

የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው። ወደ ዕብ 4:12 ሕይወትና ቅዱስ መንፈስ አለበት። ዮሐ 6:63 የእግዚአብሐር ቃል በሚቆራርጥ ሰይፍ የተመሰለው ክፉ ኃጢያትን ስለሚያስወግድ ሲሆን አንደኛው የተመሰለው ደግሞ በልባችን ተዘርቶ ፍሬ ስለሚያፈራ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል እንደመስታወት ኃጢያት ነውራችንን ያሳየናል። በዚህም ነውራችንን ተረድተን በንሰኃ እናስወግደዋለን (ያዕቆብ 1:21)

የእግዚአብሔር ቃል የሕይወታችን መመሪያ ስለማድረግ በንጉስ ዳዊት የተፃፈው መዝሙረ ዳዊት 119 : 3 ይገልጽልናል። "አቤቱ የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ፣ ሁል ጊዜም እፈልገዋለሁ እንዳስተውል አድርገኝ ሕግህንም እፈልጋለሁ። በፍጹም ልቤም እጠብቀዋለሁ እርሱንምን ወድጃለሁ የትዕዛዝህን መንገድ ምራኝ"

የእግዚአብሔር ኃይል መገኛው ብርቱ የፀሎት ሕይወት ነው

ማንኛውም ሕዝብና መንግስት ወደ ኋላ ከሚመልሰው ጀርባን ለእግዚአብሔር ከመስጠት የከፋ ነገር የለም።

ብቃት ያለው የእምነት አንቀጽ የተጠናከረ ቤተክርስቲያንና ወንጌሉን የማከለ ሥርዓት ቢኖርም በብርቱ ፀሎት እስካልተደገፉ ድረስ የሰዎችን ሕይወት የሚለውጡ አይሆኑም።

በነቢያቱና በሐዋርያቱ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው በብርቱ ፀሎት በተጋደሉበት ወቅት መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል። (ኤርሚያስ 29:13)

ለኤልያስ የእግዚአብሔር ክንድ የተገለጠውና የበዓል ነቢያትን መስዋዕት መንፈስ ቅዱስ የበላው በብርቱ ፀሎት ነው። ሃና ሰካራም ተብላ በነብዩ ኤሊ እንድትወቀስ ያደረጋትና ሣሙኤልን የመሰለ ትልቅ ነብይ ያስገኘላት ብርቱ ፀሎት ነው።

የእስር ቤት ሠንሠለቶችና በሮች ለጴጥሮስና ለሲላስ የተከፈቱት በጸሎት ነው። ዛሬም የራሳችንም ሆነ የሀገራችን ቀውስ የሚወገደው በፀሎት ነው።

በጸሎት የሚገኝ ኃይል

(በቻርለስ ስፐርጂን)

"በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ፤ ይሆንላችሁማል" (ዮሐንስ 15:7)

በክርስቶስ ለታመኑት ይህ ልዩ የኃይል ስጦታ ለምን ይፈቀዳል?

በእኔ ብትኖሩ ብሎ ጌታ በቃሉ የገለጸልን በጸሎትና በቃሉ ከእርሱ ጋር የመጣበቃችን አስፈላጊነትን ያሳያል። የጌታን ቅባት ቅድስናና ምህረት በደሙ ኃይል ለማግኘት ጭምር ጸሎት ብቸኛ መሣሪያ ነው። ኃጢያታችንን በመስቀል ላይ በራሱ ደም ያስወገደልን። ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን የሰጠውን በረከት የምንቀዳጀው በጸሎት ነው(ኤፌሶን 2:6)።

በክርስቶስ መሳት የምንገኘውም በጸሎት ሕይወት ስንገኝ ነው(ቆላስያስ 1:14)። የማንኛውም ሰው እምነት ጸንቶ የሚቀጥለው በጸሎት ይሆናል። "በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል" ብሎ ጌታ ያስተማረን የሚፈጸምልን በጸሎት ነው(ማርቆስ 9:23)

ጌታ መንፈስ ቅዱስ ሊነገር በማይቻል መቃተት ለእኛ የሚማልደውና በእኛ የሚሰራው በጸሎት ብቻ መሆኑን ቅዱስ ቃሉ ይመሰክራል። "እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና። ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል" (ሮሜ 8:26)

ኃይል የእግዚአብሔር ነው

እግዚአብሔርን እንደ ባለመሉ ኃይልና ባለስልጣን እስካልተቀበልነው ድረስ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ማንነት አንረዳም። የእግዚአብሔር ኃይል ልክ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔር ማንነት ትርጉም አይኖረውም።

የእግዚአብሔር ኃይል ፍፁም ዘላለማዊና ሊመረመር ሊደረስበት የማይችል ነው። " እግዚአብሔር አንዴ ተናገረ እኔም ሁለቱ ሰማሁ" (መዝ 61:11) እግዚአብሔር እንደተናገረ የሚለው ቃል ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ምንም ታላቅ ነገር እንደሌለ ያመላክታል።

እግዚአብሔር አንዴ ሲናገር ታላቅ መሆኑን ዘላለማዊ መሆኑን ቅዱሳን ያመኑና የተቀበሉት ትናንት ነቢያቱና ሐዋሪያቱ ዛሬ አማኞች ሁሉ በረከቱን ኃይሉንና ቅድስናውን ይቀበላሉ።

ከተጣለበት ከተራቡ አንበሶች አፍ የተረፈው ዳንኤል፣ በለምጥ የተመታውና ጌታ ያነፃው ሕመምተኛ ድውይ ከተቀበረበት "ተነሳ" ተብሎ የተነሳው አልዓዛር እግዚአብሔር አንዴ ሲናገር ሰምተው በረከቱን ከተቀበሉት ውስጥ ናቸው። እኛም ዛሬ ቃሉን ሰምተን በእምነት ብንታዘዘው ለበረከቱ እንበቃለን።

የእግዚአብሔርን ኃይል የማመን ምክንያቶች

በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ" (ኤፌሶን 6:10) በኃይሉ ችሎት ምን ማለት ነው? አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ብርቱና ኃያል ተብሎ ይገለፃል። ይህ አባባል የጌታን ኃያልነትና ግርማ ያመለክታል።

አንድ አማኝ ሰው የእግዘአብሔርን ኃይል ለመቀበል በእግዚአብሔር ባለሙሉ ኃያልነት ሊታመን ይገባዋል። ከማመንም በላይ በሙሉ ኃይልና ተግባር ሰው የእግዚአብሔርን ኃያልነት ሊቀበል ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር "የሚገጥመን ፈተና ድካምና መሰናክል የሚያውቅ በመሆኑ ችግራችንን ይረዳል::::

አባት ትንሽ ልጁን በቀስታ እንደሚመራ ሊወድቅ እንደሚያነሳውና እንደሚሸከመው

እግዚአብሔር አማኝ ልጆቹን ይንከባከባቸዋል።

እግዚአብሔር ይህንን ድጋፉን በድካማቸው ጊዜም ለእምነት አባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለሙሴ፣ ለኖህና ለተቀሩትም አሳይቷል፤ ለእኛም ያሳየናል።

እግዚአብሔር ይህን ተራዳኢነቱንና ድጋፉን ለሕዝቦቹ ያሳያል(ዘጸአት 6:3) የእግዚአብሔር ረጅነትና ታዳጊነት በዘመናት ሁሉ በጉዳት ላይ ላሉት ልጆቹ ቤተሰቦቹ ሕዝቦቹ ይገለጻል(ዮሐንስ ወንጌል 11:32፣ ሉቃስ 1:18)።

እግዚአብሔርን እንደቤተሰብ እንመነው

ልጆች መታመንን በምሳሌ ሲመለከቱ ይረዱታል (ምሳሌ 22:19)። ወላጆች ልጆቻችሁ መንፈሳዊ ልምምዶችን አይረዱም ብላችሁ ፈጽሞ እንዳታስቡ። በግል ሕይወታችን ልጆቻችን ሊረዱት አይችሉም በምንላቸው ጉዳዮቻችን ከእኛ በበለጠ ልጆቻችን ተረድተውት እኛን ያስደነቁበት ጊዜ አጋጥሞናል።

በቤተሰባችን መካከል በእግዚአብሔር መታመናችንን በየቀኑ የጸሎትና የቃል ሕይወታችንና በምስክርነታችን እንግለጸው። በገንዘብና በብልጽግና የሚታመኑ ይጠፋሉና መታመኛችን ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ይሁን(ምሳሌ 11:28)።

ጣዖት የተባለው ነገር በሰው እጅ ለተሰራው ምስልና ቅርፅ በብሉይ ኪዳን የተሰጠ ስያሜ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ማንኛውም የጌታን ስፍራ የሚወስድብንና የሚሻማብን ነገር ሁሉ ሊወገድ፣ ሊስተካከልና ጌታ እግዚአብሔር ሊቀድም ተገቢ ሥፍራውን ሊይዝ ይገባል(1 ቆሮንቶስ 10:7)። የሚቀርቡን የሚረዱን ቢሆኑም እንኳ ከጌታ ይልቅ በሰዎች አንታመን መታመኛችን ሁልጊዜ ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ይሁን (መዝሙር 118:8፣ ዮሐንስ 14:10)

የምስክርነት ኃይል

በአንድሪው ሙሬ

"እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" (ሉቃስ 24:49)

ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ ኃይል እስኪቀበሉ ድረስ እንዲቆዩ አሏቸዋል። እነዚህ አቅመ ደከሞች በተያዙበት ወቅት የካዱትና የራቁትን እንዴት "ቆዩ" ሊላቸው ቻለ?

ጌታችን አማኝ ልጆቹ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንዲጎበኙ ድካማቸውን በመረዳት በጥሞና በጸሎት እንዲቆዩ የሚፈልግ አምላክ ነው። ደቀመዛሙርቱ ጌታን በሚገባ የሚያውቁት ቢሆንም ዘወትር ከሚናገራቸው ቃላት እንደምንረዳው ሙሉ በሙሉ የሚረዱት አልነበሩም። ነገር ግን በቆይታ ሂደት መንፈስ ቅዱስ በሙላት ሲፈስስባቸው የጌታን ማንነትና ሀሳቡን ሙሉ በሙሉ ለማወቅ ደርሰዋል። እነዚህ የክርስቶስ ተከታዮች ከመመስከራቸው በፊትም ሆነ በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለምሥክርነት ሕይወት ረድቷቸዋል፣ ተጠቅሞባቸዋል። "ኃይልን ትቀበላላችሁ" በሚለው ቅዱስ ቃሉ መሠረት ደቀመዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን በመቀበል ሞትንና እስራትን ሳይፈሩ ለእርሱ ለመመስከር፣ ሌሎችን ወደ መንግስቱ ለማፍለስ በቅተዋል። ዛሬም ኢየሱስ ክርስቶስ ያው ነው። የእርሱን ማነነት ለመመስከር ኃይሉ ያስፈልገናል(ሐዋርያት 1:8)

በሴሪላንካና በኢትዮጵያችን ላለው ብርቱ የፖለቲካ ቀውስ እንጸልይ

የምጽአቱ የምሥራች ዓለም አቀፍ አገልግሎት በቅርብ ጊዜያት ወስጥ ከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ለገባቸው የእስያ ሀገር ሴሪላንካ ብርቱ ጸሎት ጠይቋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያም እንደዚህ ባለ ቀውስ ውስጭ በማለፍ ላይ ስላለች መፍትሔውን ጌታ እግዚአብሔር ይሰጠን ዘንድ በብርቱ እንጸልይ።

የሲንሄል ህንድ የምጽአቱ የምስራች ምንም እንኳን የማሳተሚያ ወረቀቶችና የሕትመት ዋጋ ቢጨምርም ቀጥሏል። የአማርኛው የምጽአቱ የምስራች የአንባቢያን መዋጮና ተሳትፎ ምንም ቢቀንስ የበጎ ፈቃድ አስተባባሪና በነጻ ተርጓሚው አዶ/አደፍርስ ሀብቱ/ ያለመታከት ከግል ገቢው ወጭ በማድረግ ህትመቱ ይቀጥል ዘንድ ከደጋፊ ባለቤቱ ፋንታዬ ግርማ ጋር ቀጥሏል።

የሰዎችን ልብ የሚያማልል "ትበለጽጋላችሁ" የሚል ተስፋ ብቻ ከመስጠት የበረከት እንቅፋቶች ኃጢያትና እርሞችን በጌታ ቃል እየገለጠ ለምድርም ሆነ ለሰማይ በረከት የሚያበቃውን የምጽአቱ የምስራች አገልግሎትን እንቀጥላለን በጸሎትም ለሀገራችን ኢትዮጵያ እንጋደላለን። ምንም ተስፋ አንቆርጥም። (መዝሙረ ዳዊት 68:34፣ 68:31)

ፍቅር በልዩ ከፍታው

በቻርለስ ስፐርጆን (ቅድ 955/956)

"አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ።"

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወደን ያላንዳች ጥርጣሬ እንመነው። እኛ በእርግጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሆንን እርሱ በትክክል ያድነናል። እስከመጨረሻው ያፈቅረናል። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር በልዩ ከፍታ ላይ ያለ ልዩ ፍቅር ነው። ጌታችን ለልጆቹ ሥፍራ ያለው ሲሆን አብ እግዚአብሔር እንደሚወደኝ እወዳችኋለው ባለው ቃሉ መሠረት በፍጹም ፍቅሩ ይወደናል።

ከመጀመሪያውም እግዚአብሔር ልጆቹን ያፈቀረን ገና ከመጀመሪያው ከፍጥረት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል በሆነ ፍቅር ይወደናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠው አምላክ ይህን ከፍታ ላይ ያለ ፍቅሩን ለአማኝ ልጆቹ የሚያሳየው እኛም ሌሎቹን እንደዚህ እንድናፈቅር ነው (ፊልጵስዩስ 2:6)።

በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባን ፍቅር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ሰጥቷል (ኤፌሶን 5:34)። በዚህ የከፍታ ልዩ ፍቅር እግዚአብሔር አማኝ ልጆቹ በዓለም መካከል ያጡትን ፍቅር መቀባበልና መደጋገፍን ሰላምን ያጎናጽፋቸዋል። እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ገና ከመጀመሪያ በብሉይ ኪዳን በመጀመሪያዎቹ መጻሕፍቱ ገልጾታል (ዘዳግም 7:7)። "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና፤ በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ መረጠህ"።

ለእግዚአብሔር ይህን ትልቅ ፍቅሩን በከፍታ ላይ ያለውን በመጨረሻው ዘመን ከሴት የተወለደ ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመላክ ለሰው ዘር ኃጢአት የሚገባውን ቅጣት በመስቀል ስቃይ ሞት

የከፈለው በትልቅ ፍቅሩ ነው። የራስን ሕይወት ለሌላው ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለም። ዮሐ 15፡13 “ ነፍሱን ለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም” በሌላ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ይህ የእግዚአብሔር ልዩ የከፍታ ፍቅሩ በደል የሌለው ለበደለኞቹ ሕይወቱን ሰጠ ብሎ በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡18 የተገለፀው ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ፍቅር የራሱን ሕይወት በራሱ ፍቃድ በስቅላት በሮማው ቄሳር ሥርዓት የሰጠው የክርስቶስን ልዩ ፍቅር ይገልጽልናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥንቱ ብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስከ ዘመናችን በአዲስ ኪዳን ሕዝቦቹ የሚሰጠው አገልግሎት ምድራዊ ስኬትንም ሆነ ሰማያዊ መባረክን ያስገኛል።

ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚኖረን ቅንጅትና ህብረት ከማያምኑት ጀብደኞች ይልቅ በእውነት ለጌታ የሚተጉትን በማየት ላይ እንገኛለን።

የክርስቶስ ፍቅር ትዕቢትና ጥላቻን በማስወገድ የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ያደርገናል። ስለዚህ ጌታ ቅዱስ መንፈሱን ነፍስ ሥጋችንና አእምሮአችንን ይቀድሳልና እንማጸነው።

በፍቅር እንኑር

የእግዚአብሔር አምላክነት ልዩ ባህርይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን በማፍሰስ በመስቀል ላይ ሕይወቱን የሰጠበትና መንፈስ ቅዱስ ዘወትር የሰው ዘርን የሚወቅስበት ዋነኛ ምክንያት የአምላክ ፍቅር ነው።

ይህ ከእግዚአብሔር የሆነው ፍቅር ለመላው የፍጥረት ዘር በጌታችን ወንጌል የተገለጸ ሲሆን ይህ ፍቅር እግዚአብሔርም ሆነ ፍጥረቱን በሙሉ ልብ መውደድ መሆኑን ጌታ ያስተምረናል። ዮሐ 3፡16 ማቴ 22፡37 ዮሐ 13፡ 34 ሮሜ 13፡10 ቆላስ 3፡14

ጌታ እግዚአብሔር ስለ ፍቅር የሰጣቸው እዕዛዛት በሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸ ሲሆን ይህንን ፍቅር በምሳሌነት የማሳየት ቀዳሚ ኃላፊነት ያለባት የቅዱሳን ህብረት የሆነችው ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት።

ይህን ኃላፊነት ለአብያተክርስቲያናት ዛሬም ጌታ ማሳሰቢያውን ይሰጣል። ራዕይ 2፡4

ፍቅር አልባ የሆነች ቤተክርስቲያን ወይም የክርስቶስ ማህበር ልክ ህይወት እንደሌላው የፕላስቲክ አበባ ስትመስል ቅዱስ ቃሉ ደግሞ በከንቱ የሚንሿሿ ብረት ወይም የናስ ፀናጽል ይሆናል 1ቆሮ 13፡1።

ፍቅር በአማኙ ሕይወት ለመኖሩ ማስረጃው በአንደበቱ ከሚገለጽ ፍቅር ያለፈ በሕይወት የሚገለጽ መልካም ምግባር ነው። ለማንኛውም የሰው ዘር ወይም - ፍጥረት በተለይም - ለአማኙ ማህበረሰብ ፍቅርን መግለጽ ከአማኙ ከቤተክርስቲያን የሚጠበቅ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። 1ዮሐንስ 3፡16

መልካም ወይም ክፉ ነገር ወደ ሆዳችን ሲገባ ሽታው በአፉ ወጥቶ ለሌሎች የሚታወቀውን ያህል የመልካም ሥራ ውጤትም በልባችን ካለው ሀሳብ ይመነጫል። የመልካም ሥራ ፍሬ በሕይወታችን እንዲገለጥ የጌታን ቅዱስ ቃል ዘወትር እየተመገብን የሚያሳስበን የሌሎችን ጉድለት ለመቅረፍ ልንተጋ ይገባል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ እኖራለሁ ብሎ በወንጌሉ ቃል የገለጸው የእግዚአብሔር ፍቅር የሚወልደው መልካም ሥራ፣ ለሌላው ሰው ወይም አማኝ በተግባር በመግለጽ ይሆናል። ዩሐ 17፡26

በዚህ ወቅት በሀገራችን ወጣቱ ትውልድ መልካም ሥራ እንዲሠራ በቤተክርስቲያን በመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) የሚዘገበው ዘለአለማዊ የሆነው ጌታ መንፈስ ቅዱስ የሚልከውን ቅዱስ መንፈሰን ኃይሉን መጀመሪያ በአማኞቹ ልብ ውስጥ ሲያኖር ነው።

በፍቅር ዘወትር መኖር የምንችለው የእግዚአብሔርን ፍቅር በተንኮል በማታለል ወይም በጉዳት ከአማኞች ሊነጥቅ በሚከናወን የኃጢያት ሥራ በመራቅ ነው። የእግዚአብሔ ቅዱስ መንፈስ በአማኞቹ ሕይወት ውስጥ ሥራውን ሲቀሰቅስ ብዙ ተግዳሮቶች ቢኖሩም አማኝ በንስሃና በምልጃ ፀሎት ዘወትር ሊተጋ ይገባዋል። በመንፈስ ቅዱስ ቀስቃሽነት አማኞች በበጎ ሥራ የሚተጉት ክርስቶስ በእነሱ ውስጥ ከመኖሩ የተነሳ ነው።

ፍቅር የእግዚአብሔር ምርጥ ስጦታ ነው

የጌታ ሐዋርያ ጳውሎስ ስለመንፈስ ቅዱስ አስራር ብዙ ካስተማረ በኃላ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ የበላይ ስለሆነው ስለፍቅር ምርጥ መንገድ መሆኑን አስተምሯል(1ቆሮንቶስ 13፡1) ።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለመንፈስ ቅዱስ አሰራርና ፍሬዎች ካስተማረ በኃላ አማኞቹ ይህን ሕያው አገልግሎት እንዲቀጥሉ በማሰብ በአጽንኦት መስክሯል(1ቆሮንቶስ 12፡9፣ ኤፌሶን 4፡11)።

ማንኛውም ጉባኤ በልዩ ልዩ እውቀት ሲባርክ በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የበለጠ የወገኖችን ልብ የሚዘልቅ አገልግሎት ይካሄድ ዘንድ ለጌታም ለሰውም በሚገልጽ ፍቅር ሊካሄድ ይገባዋል። (ማቴዎስ 22፡37)

ስለዚህ የእግዚአብሔር ምርጥ ስጦታ ስለሆነው ስለፍቅር በዓመት 365 ቀናቱን በሙሉ በሰብክም የማያልቅ እጅግ የተትረፈረፈና ልዩ ብቃት ያለው የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (1ቆሮንቶስ 13)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በጽናት የሚገለጸውና ይህ ፍቅር መጀመሪያ የተገለፀው ፍቅር ከሆነው እግዚአብሔር ሲሆን ይህ ፍቅር ለሰዎች ሊገለጽ የሚገባው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው ገላቲያ 5 1ዮሐንስ 1፡16

ጌታችን ደቀመዛሙርቱና ሌሎችን ተከታዮቹን ሲያስማራ እንደሚወዳቸው የተናገረው ትምህርት ይሁነን ዮሐ 13፡34

ፍቅር በሌለበት ሥፍራ ማንኛውም የእግዚአብሔር ሥራም ሆነ የፀጋ ሥጦታ የከንቱ ከንቱ ይሆናል(1ኛ ቆሮንቶስ 12፡31፣13፡1)። በሰማይ ቋንቋ በልሳን መናገር ቢሆን ወይም የሕይወት መስዋእትነት ቢሆን ፍቅር ከሌለበት ከንቱ አገልግሎት ስለሚሆንብን ከማገልገሉ ከመዘመሩ ከመምራቱ በፊት ለእግዚአብሔርና ለፍጥረቱ ፍቅር ይኖረን ዘንድ እንፀልይ እንማልድ።

ፍቅር የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ከሚገነቡት ስጦታዎች ሁሉ እጅግ የላቀው ነው (ኤፌሶን 4፡11)።

የፍቅር ስጦታና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚኘው በክርስቶስ በሚኖር እምነታችን ነው። (1ቆሮንቶስ 12፡9)

የእግዚአብሔርን ባህሪያት ልንጋራ ልንሳተፍ ከሚገባቸው ዋነኛው ፍቅር የሆነውን ጌታ በፍቅር ሕይወት ሌሎቹን በመድረስና በመንከባከብ ነው። (1 ዮሐንስ 1፡8)

አብርሃም አንድ ልጁን ለእግዚአብሔር ለመሰዋት በብሉይ ኪዳን ዝግጁ እንደነበረውና እግዚአብሔርም ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ሞት የቀጣው ለሰው ዘር ሁሉ ካለው ፍቅር የተነሳ ነው። ይህን ፍቅር ጌታ የራሱን ሕይወት ለሌለው ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለም የሚለንን ተረድተን በጌታ ፍቅር ሰዎችን ሁሉ ለማድረስ እንትጋ (ሐዋርያት 5፡1)።

በቀራኒዮመስቀል ላይ ከተገለፀው ፍቅር በላይ ፍቅር የለም

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ ሶስት ላይ የዘረዘረው በመስቀል ላይ ከከፈለውና ምንም አቻ ከማይገኝለት ፍቅሩ የሚመነጭ ነው(ኤፌሶን 2፡4)።

በቀራኒዮ መስቀል ላይ የተከፈለልን መስዋእትነትን በሚገባ ለመረዳት በደላችንና ኃጢያታችንን በሕጉ መሰረት ሊፈጽምብን የተገባውን ቅጣት እስካልተረዳን ድረስ ይህን ልዩ ፍቅር ምን ጊዜም ልንረዳ አንችልም።

የራሳችንን የገዘፈ ኃጢያትና በደል በእውነተኛ ንስሃ ሳናስተካክል የሌላውን ኃጢያት ልንጠቁም ልንፈርድ የሚዳዳን ይህን የቀራኒዮ መስቀል ሚስጢር ካለማወቃችን የተነሳ ነው።

በቀራንዮ መስቀል ላይ ጌታችን ለኃጢያታችን ሁሉ መስዋዕት ሆኖ የመስቀል ቅጣት ሞትን የተቀበለልን በቅዱስ ቃሉ የተዘራ ስንዴ በምድር ላይ ተዘርቶ ከበሰበሰ በኋላ ድጋሚ ፋፍቶ በማደግ ትንሳኤ ከሚያገኘው ጋር የሚመሳሰል ድርጊት ነው(ዮሐንስ 12፡23)።

የመስቀሉ ፍቅር በሚገባ ከገባን በእምነታችን የሚደርስብንን የዚህ ዓለም ስቃይና መከራ ሁሉ በደስታ የምንቀበል እንሆናለን (1 ጴጥሮስ 4፡12)።

የምድር ምቾትን በማሰብ በዚህ ምድር ላይ በደስታ መኖርን ከተመኘን የመስቀሉ ፍቅር አልገባንምና የመስቀሉን ፍቅር ጌታ እንዲገልፅልን እንፀልይ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ባህርያት

"እናንተ በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ ናችሁ" (ማቴዎስ 5፡14)። ክርስቲያኖች ዓለሙ ሁሉ የሚያውቃቸው የሚመለከታቸው በመሆኑ ከሚደርስብን ነቀፋና ስድብ ለመጠበቅ በመንፈስ ቅዱስ የተመራና በቅድስና የተሞላ ኑሮ ሊኖረን ያስፈልጋል።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ ቅንአት ጥላቻ የማይኖረው ይልቁንስ ፍቅርና ሰላም የበዙለት መሆኑን ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (1ኛ ቆሮንቶስ 13)።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ እውነተኛ ልምምዶችና የጸጋ ስጦታዎች በሕይወቱ የሚገለጽበት ው። እግዚአብሄር የሚገስጸን የሚቆጣን የሚያስተካክለን ከበዛው ፍቅሩ የተነሳ ነው(ሉቃስ 11፡13፣ ገላትያ 2፡22)።

ለመንፈስ ቅዱስ በተጠማና መላቱ እንደሚያስፈልገው ጌታ የገለጠለት አማኝ መንፈስ ቅዱስን በጸሎት ከጌታ በመቀበል መገስገስ ይችላል(ሉቃስ 11፡13)።

የጌታችን የመቤገቦት ፍቅር በተጨባጭ ባሉብን መንፈሳዊም ሆነ ስጋዊ ወይም አካላዊ እንቆቅልሾች ላይ ስልጣን ያለው ኃይል ነው።

ከፈተናና ከችግሮቻችን የተነሳ ባህርያቶቻችን መቀየራቸው ሲታወቀን ወይም ሌሎቹ ሲነገሩን ከመንፈሳዊ መሪዎች ጋር በመጸለይ በመትጋት ችግሮቻችንን በጌታ ማስቀረፍ እንችላለን።

ለፍቅር እንጸልይ

ለጸሎት ከመንበርከካችን በፊት በልባችን አንዳች ቂም እንዳይኖረን ክርስቶስ የሞተላቸውን ሁሉ ይቀር በማለት በፍቅር እንድንኖር የጌታ ቃል ያሳስበናል(1 ተሰሎንቄ 3፡12፣ ማርቆስ 11፡25)።

ከዚህ የተነሳ ለፍቅር መፀለይ የጸሎቶች ሁሉ ቅድሚያ ርዕስ መሆን እንደሚገባው የታመነ ነው። ለማንኛውም ችግር መፍትሄና ለበረከት መገኘት ለድል ሕይወት ጸሎት ቁልፍ የመሆኑን ያህል ለጸሎት ቁልፍ የፍቅር ልብ መሆኑን እናስተውል።

ስንት ጊዜ ይሆን ጌታ መንፈስ ቅዱስ ለጸሎት ስንበረከክ የሚጎዱንን የሚቃወሙን የሚያሳድዱን ሰዎች ወደ እኛ ልብ የሚያመጣው? ይህ ድንቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስለሆነ ማንኛውም የእኛ ይቅርታ የሚያስፈልገውን ግለሰብ በፍቅር መንፈስ ይቅር በማለት ጸሎታችን መልስ ያገኝ ዘንድ ለፍቅር እንጸልይ።

ሐዋርያው በሌላ ክፍልም ልባችን በፍቅር ሲሞላ የሕይወት ትርጉም እንደሚሳካ ልባችንም በእምነት እንደሚጽናና ያስተምረናል (ቆላስያስ 2፡1)።

ስለዚህ ለግለሰብ ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብ፣ ለሀገርና ለመላው ዓለም ጸሎት ስናቀርብ በፍቅር ልብ ጌታ እንዳስተማረን በድል እንዲጠናቀቅ ለፍቅር እንጸልይ። ጌታ የፍቅር መንፈሱን ያፍስስልን።

ኃጢያትና ድካምን እያሸነፍን ወይስ እየሸፈንን?

ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ የሰጠን ተስፋ ኃጢያትና ድካማችንን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለጌታ በመናዘዝ እንድናሸንፍ እንጂ ምንም ጉድለት እንደሌለብን እንድንሸፋፍን አይደለም።

እግዚአብሔር በፍቅሩ ብዛት እራሱ ኃጢያታችንን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመሸፈን ለድል የሚያበቃን፣ የሚያነጻን፣ የሚቀድሰን በጸጋውና በምህረቱ ነው።

በአንድ ሰው አዳም ምክንያት ወደ ሰው ዘር የገባው ኃጢያት በአንድ ሰውና አምላክ በሆነው በክርስቶስ ኃጢያታችን ተወግዶ የእግዚአብሔር ልጆችን ሆነናል(ሮሜ 5፡17)።

የሁሉም ሰው ስራ በጌታ ፊት የተገለጠ በመሆኑ በጣፋጭ ቃላት በመስዋእት በማካካስ የጌታን ልብ ማስደሰት አንችልም። ጌታ እጅግ የሚያስደስተው በእኛ መታዘዝና ከክፉ መንገዳችን በመመለስ ነው(1 ቆሮንቶስ 3፡13፣ 1 ጴጥሮስ 4፡8)

በጌታ በተሰጠን ትልቅ እድል በእምነት የዘላለም ክብሩ ተሳታፊዎችና ወራሾች ሆነናል ። ለዚህ በመንፈስ ቅዱስ በታተምንበት ምልክት ወደፊት ልንገሰግስ ይገባል(ፊልጵስዮስ 3፡14)።

ጌታ ገና ኃጢያተኞች ሳለን በምህረቱ ከወደቅንበት ያነሳንን ዘወትር በማሰብ ላሬ ለወደቁት ልንራራ ልንጸልይና ልንመስላቸው ያስፈልጋል(ሮሜ 5፡8)

እግዚአብሔር የእኛን ኃጢያት በልጁ በክርስቶስ ደም እንደሸፈነ እኛም የወንድሞችና እህቶቻችንን ነውር በጸሎት እንሸፍን፣ በሚስጢር እንያዝ፤ ጌታ በቅዱስ መንፈሱ እንዲያሸንፉ እንማልድላቸው።

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ

ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ፍሬና የጸጋም ስጦታ ነው። በፍቅር ስጦታ ድሮ የበደሉንን ዛሬም የሚያሳድዱንን፣ የሚጠሉንን እንድንወድ ከጌታ የተሰጠን የፍቅር ስጦታና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እጅግ ይጠቅሙናል (ገላትያ 5፡22፣ ማቴዎስ 25፡35)።

ከፍቅር የተነሳ እናት የቆሸሸ ልጇን አጥባ ዘወትር ተንከባክባ እንደምታሳድገው ጌታ እኛን እነዲሁ እንደሚንከባከበንና እንደሚያሳድገን እንረዳ በዚሁ መልኩ እኛም ሌሎቹን በፍቅር የፀጋ ስጦታና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ልንከባከብ፣ ልንከታተልና ልናሳድግ ይጠበቅብናል።

ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር በተፈጥሮ እንስሳት ለልጆቻቸው ከሚያሳዩት እጅግ የላቀ ልዩ መለኮታዊ ሁኔት ነው። ሰዎች ለተለያዩ ነገሮች ፍቅር እንዳላቸው ሲናገሩ የምንሰማ ሲሆን ከእግዚአብሔር የተገኘው ፍቅር ግን በግሪክ ቋንቋ አጋፔ የተባለው ራስን መስዋእት የሚያሰጥ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ በመስቀል ላይ የገለጠው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ብቻ መረዳት የሚቻለው ፍቅር ነው።

ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ተራ መጀመሪያ የተጠቀሰው በመንፈስ ቅዱስ አሰራር ፍቅር ተቀዳሚና ልዩ ስጦታና ፍሬ መሆኑን ለማሳየት ነው።

የክርስቲያኖች ፍቅር መንፈሳዊ ፍቅር በመሆኑ ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ይህንን ዘላለማዊ ፍቅር እንጠማ እናስፋፋው።

የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል።

የክርስቶስ ፍቅር ግድ የሚላቸው ክርስቶስን በሙሉ ልባቸው የተቀበሉና በክርስቶስ ፍቅር በየቀኑ የሚኖሩ አማኞች ብቻ ናቸው።

መንፈስ ቅዱስ ጌታ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ በተገለጸበት ሁኔታ በበአለ ሃምሳ ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ወቅት ተከስቷል።

ይህ የክርስቶስ ፍቅር አንዳች የዘር፣ የቋንቋ፣ የብሔረሰብ ልዩነት ሳይገድበው ዛሬም በሐዋርያቱ ላይ እንደሠራው በሚያምኑበት ላይ ይሠራል። የመገናኛ ብዙኃን ሚዲያ ክፋትን ብቻ ለመዘገብ የሚተጉበት በመሆኑ እንጂ የክርስቶስ ፍቅር ግድ የሚላቸው ዛሬም በመላው ዓለም በሀገራችን ኢትዮጵያም ጭምር ይገኛሉ። የዘመኑ እርም ሳይዛቸው የሰውን ዘር ሁሉ በክርስቶስ ፍቅር ያፈቅራሉ፣ ይከባከባሉ ያገለግላሉ።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የኢንዱ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ማህበር የአካል ክፋይ መሆኑን በማወቅ ለሌሎች ክርስቲያኖች ምንም ያህል የአመለካከት የዶክትሪን የዘር ልዩነት ቢኖር መጸለይ፣ ማፍቀር፣ ጎብረት ማድረግ ኃላፊነት አለብን(1 ቆሮንቶስ 12፡12)።

ማንኛውንም ክርስቲያን ሆነ የሰው ዘር የክርስቶስ ፍቅር ግድ የሚለው ሰው ሊጎዳ፣ ሊነቅፍ አይገባውም። የፍቅር ጌታ ክርስቶስ እንዳስተማረን ለራሳችን ሊደረግ የምንፈልገውን ሁሉ ለሌሎች እናድርግ (ማቴዎስ 7፡12)።

በሁሉም ነገር ማስተዋል ይኑረን

አማኞች በሕይወታቸው ሁሉ ሩሯቸው ሁሉንም ነገር በማስተዋል በመፈጸም መሆኑን ቅዱስ ቃሉ ያስተምረናል። በእምነት መጠንከር የሚቻለው ነገሮችን በማስተዋል በጸሎትና በጌታ ቃል በየእለቱ በመሞላት፣ በእምነት በመመላለስ በመኖር ነው(1 ቆሮንቶስ 16፡13፣ 2 ጢሞቴዎስ 6፡11)

ክፉ አንደበት ሀሜት ስድብ ቅድስናችንን ስለሚጎዳ ልንጠነቀቅና ልንርቅ ይገባናል(ሮሜ 13፡8፣ ገላትያ 5፡19)።

ይልቁንም ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ የሚቀጣጠሉ ፍቅርና ምህረት የሚበዛላቸው የሰላም፣ የእርቅ፣ሠራተኞች እንዲሆኑ ቅዱስ ቃሉ ያሳስባል(ሮሜ 12፡7፣ ገላትያ 5፡23)።

አማኞች ከማስመሰል የግብዝነት ሕይወት የጠሩ እውነትን እውነት፣ ኃጢያትን ኃጢያት ማለት በድፍረት የተለማመዱ መሆን አለባቸው።

ዘመናችን በጥቅም ፈላጊነት በራስ ወዳድነት በዘረኝነት በወገንተኝነት የተሞላ ቢሆንም የክርስቶስ ተከታዮች ከዚህ ዓለም ክፉ አሰራር ነጻ የወጡ የእውነት ልጆች፣ የሰላም ልጆች ናቸው(ማቴዎስ 22፡36፣ ወደ ዕብራውያን 12፡14)።

እስከመጨረሻው ድረስ በጀመርነው እምነት የክርስቶስን ፍቅር በመከታተል በዚህ ክፉ ዓለም በሁሉም ነገር ማስተዋል እንድናገኝ ጌታ ይርዳን!

በእውነተኛ ፍቅር ክርስቶስን ስለመጠባበቅ

በዚህ የምጽአቱ የምስራች የወንጌል አገልግሎት ሰዎች የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እንዲጠባበቁ የምናስተምረው በፍቅርና በእውነት እንዲኖሩ ነው።

የተባረከ ተስፋችን ክርስቶስን ስንጠብቅ ኑሯችን ፣ ንግግራችን፣ ማኅበራችን ሁሉ በእውነተኛው ግብዝነት በሌለው ፍቅር በመመራት ነው(ቲቶ 2፡13፣ 1 ዮሐንስ 4፡10)።

እውነተኛ ፍቅር ሙሉ በሙሉ ከሥጋ ስራዎች የተለየ ነው(ገላትያ 5፡19) በእውነተኛ እምነት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚጠባበቁ ሁሉ እውነተኛውን ፍቅር ሊለማመዱ ይገባል።

በዚህ እውነተኛ ፍቅር በጌታ በመታመን በእምነት የምንጠብቀው አንዳች ጉድለት እንዳይገኝብን ከሠይጣን ከዓለምና ከሥጋችን ጋር በየቀኑ በመፋለም ነው(2 ጴጥሮስ 3፡14)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳዘዘን ወንጌሉን በማስፋፋት ያለንን የሰጠንን ስጦታዎች ሁሉ ሳንቀብር ልንተጋ ተጠርተናል (ሉቃስ 19፡13)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትጋታችንን ድካማችንን የሚረዳና በነገር ሁሉ የተፈተነ ከኃጢያት በስተቀር በሁሉ እንደእኛ ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑ እንታመንበት፤ የልባችንን እናሳየው።

ፍቅርን ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን ለሌሎች በማካፈል የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እንጠብቅ እርሱም ሥራችንን

ስለሚያውቅ በሁሉ ይረዳናል።(1 ተሰሎንቄ 1፡3፣ ራዕይ2፡2)

ለልጆቻችን የእግዚአብሔርን ፍቅር እናሳይ

“እስራኤል ሆይ ስማ” ብሎ የሚጀምረው የብሉይ ኪዳን የጌታ ትዕዛዝ እስራኤል ከጌታ ጋር በሌሊት ሲታገል አድሮ ስሙ የተቀየረለት በልጆች የተባረከው ያእቆብ ሲሆን አዲሱ እስራኤል በክርስቶስ ላመኑት ሁሉ የተሰጠ በመሆኑ “እስራኤል ሆይ ስማ” የሚለው ቃል የክርስቶስ አማኞችን ሁሉ ያጠቃልላል(ማርቆስ 12፡29፣ ዘፍጥረት 32፡28)።

ያለንበት ዘመን ልጆቻችን፣ ራሳችንም ጭምር የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል እንዳንሰማ አያሌ ፈተናዎች፣ ማሰናከያና ማታለያ ያለበት ነው።

ለልጆቻችን ደግሞ ከእኛ ከወላጆቻቸው በላይ የእግዚአብሔርን ቃል በቃልና በኑሮ ሊያስተምር የተገባ ማንም የለም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች እጅግ ተፈላጊና ጠቃሚ ቢሆኑም ልጆቻችን በእግዚአብሔር ቃል የማሳደጉ የመጀመሪያ ኃላፊነት የእኛ የወላጆቻቸው ይሆናል።

ልጆቻችን ሲጠመቁ ወይም ለጌታ ሲሰጡ እንደየእምነታችን የሚቆሙላቸው የሚሰየሙላቸው የክርስትና አባትና እናቶች እንደ መንፈሳዊ ተከባካቢዎች ኃላፊነታቸው ከሁሉ የበረታ ትልቅ የአደራ አገልግሎት ነው።

ስለዚህ ለእኛም ሆነ ለልጆቻችን የዘመኑ ጣኦት የእግዚአብሔርን ስፍራ የሚወስድ አንዳች ነገር እንዳይኖር እንትጋ፣ እንጸልይ፤ እናስተምር (ዘጸአት 20፡3)። የማጠቃለያ ትዕዛዛቱ እግዚአብሔርና ሰውን (ጎረቤታችንን) እንድንወድ፣ ልጆቻችንን በቃልና በስራ እናስተምር(ማቴ 22፡36)።

የጌታን ትዕዛዛት ልጆቻችንን በማስተማር ሕይወታችንን በጌታ ያማረ እናድርገው(1 ዮሐንስ 5፡3)

ሁሉም ቤተሰብ ክርስቶስን ያሳይ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕጻንነቱ ጀምሮ ለቤተሰብ ያለው ክብርና መሰጠት ምሳሌያችን ሆኖ ሁላችንም በቤተሰባችን የጌታን የፍቅር አገልግሎት በቃልና በሥራ እንፈጽም(ሉቃስ 2፡52)።

ቤተሰብ ሁለት ሰዎች ባልና ሚስት በቅዱስ ጋብቻ የሚያቋቁሙት የእግዚአብሔር ተቋም ነው። በዚህ ቤተሰብ ማእዘኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጌታ የጋብቻና የቤተሰብ ምሳሌዎችን በቅድስት ቤተክርስቲያኑ ምሳሌነት መሸራው ኢየሱስና መሸሪት ቤተክርስቲያንን በማነጻጸር ያስተማረው የፍቅርና የመታዘዝ አንድ የመሆን ትምህርትና መርህ ነው(ኤፌሶን 5፡32፣ ዘፍጥረት 2፡23)። የፍቅር አስፈላጊነትና ለጋብቻና ለቤተሰብ መሰረትነቱን ጌታችን በቅዱስ ቃሉ ያስተምረናል(ኤፌሶን 4፡32)።

ከመጀመሪያውም እግዚአብሔር ቤተሰብን የመሰረተው ለክብሩ ስለሆነ በእንዳንዱ ጋብቻና ቤተሰብ የእግዚአብሔር ክብር የበላይነትና መሪነት ሊጠበቅ ያስፈልጋል።

ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው በፍቅር በትህትና በደግነት በቅድስና ሊተባበሩ፣ ሊደጋገፉ እንደሚገባ ቅዱስ መጽሐፉ በዝርዝር ያስረዳናል። ልጆችና ሌሎች ዘመድ አዝማድም በዚህ ዓላማ እግዚአብሔር እንዲከብር፣ ቤታ ኢየሱስ

ክርስቶስ እንዲነግስና መንፈስ ቅዱስ እንዲሰራ እንዲታዘዙ እንዲተገብሩ ቃሉ ያስተምራል(ኤፌሶን 5፡8)።

ዓለም አቀፍ ምስክርነቶችና የጸሎት ርእሶች

ከጋና ምዕራብ አፍሪቃ

በየምጽአቱ የምስራች ጌታ ስለሰጠኝ መነቃቃት ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ። ከስንፍና ሕይወት ያወጣኝ የሥነጽሁፍ አገልግሎታችሁን እያደነቅሁ ጋዜጣውን በመላክ ትብብራችሁ እንዲቀጥል እጠይቃለሁ።

ከእንግሊዝ አውሮጳ

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምልክቶችን በይፋ ማየት በቻልንበት በዚህ ወቅት ይህንን የምጽአቱ አስታዋሽ ጋዜጣ ጌታ ስለሰጠን ስሙ ይባረክ! እጅግ ብዙ እጥፍ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ከሚንማር(እስያ)

በነበርኩበት የመጽሐፍ ቅዱስ ኢንስቲትዩት ይህንን ጋዜጣችሁን በማንበብ እጅግ መባረኬን እገልጻለሁ። ከተቋሙ በጡረታ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የለቀቅሁ ቢሆንም ጋዜጣውን በአዲሱ አድራሻዬ እንድትልኩልኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

ከጅማ ምዕራብ ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምስራች ለወንጌል አገልግሎቱ በጣም የጠቀመኝ የጌታ ስጦታ ነው። አሁንም እንደድሮው ቶሎ ቶሎ ባይሆንም አልፎ አልፎ ይደርሰኛል። እጸልይላችኋለሁ፤ መላኩን ቀጥሉ።

ከደሴ ሰሜን ኢትዮጵያ

በዚህ ክፉ ዘመን በመከራችን ሁሉ ያልተለየን ጌታ የተመሰገነ ይሁን። ለመንፈሳዊ ሕይወታችንም ሆነ ለሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ተሟጋች ጋዜጣችሁን አደንቃለሁ፤ እጸልያለሁ፣ መላኩን አታቋርጡ።

ከዩጋንዳ ምስራቅ አፍሪቃ

የምጽአቱ የምስራች የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ስለሚሰብክ ላመሰግን እወዳለሁ። አንዱን እትም በቅርቡ አግኝቼ ሕይወቴ ተለውጧል። ለሌሎችም አጋርቻለሁና በአድራሻዬ በመላክ የበረከቱ ቀጣይ ተካፋይ እንድታደርጉኝ እጠይቃለሁ።

ከአውስትራሊያ

የምጽአቱ የምስራች እትሞችን ለብዙ ዓመታት በማግኘታችን ጌታን እናመሰግናለን። ለአገልጉሎቱ ጌታ ከሰጠን በቅርቡ ስጦታችንን እንልካለን፣ እንጸልያለን።

ከአስመራ ኤርትራ(ምስራቅ አፍሪቃ)

የምጽአቱ የምስራች ልዩ የመንፈስ እርካታ የሚሰጠኝ ጽሁፍ ስለሆነ በየጊዜው መላኩን ቀጥሉ።

ማሳሰቢያ ለአንባቢዎች

ለሁላችሁም በግል ለመመለስ አቅሙ ስለሌለን ብዚሁ ምስጋናችን እንዲደርሳችሁ ይሁን።

የአማርኛው ትርጉም በገንዘብ እጥረት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ስለሚታተም አገልጋዮች የበጎ ፈቃደ ብቻ በመሆናቸው ለህትመቱ መስፋፋት ብርቱ ጸሎታችሁና የደጋፍ ገንዘብ እንድትልኩልን በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን።

የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ

መልዕክት ከተርጓሚውና አስተባባሪው

በቄስ/ፓስተር/ቻፕሊያን ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ

“እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፡፡ አይታክቱም ይሄዳሉ፣አይደክሙ” (ኢሳይያስ 40፡31) አዎን ዛሬም አንታክትም እንሄዳለን!

የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል መነቃቃት የትርጉም አገልግሎትን ከመጋቢት ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ በነፃ እንድናገለግል ጸጋውን መሻቱን ብርታቱን ድጋፉን የሰጠን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን፡፡

በዚህ አገልግሎት ወደጌታ መንግስት ለገቡት ከደከመባት ለተመለሱት በመነቃቃት ወደ ከፍታ አገልግሎት ለገቡትና ምስክርነታቸው በደብዳቤና በቃል በገለጹልን ወገኖቻችን የአገልግሎቱ ባለቤትና ጀማሪ ጌታ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

አገልግሎቱን በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አዲስ አበባ መጀመሪያ ስለጠየቁት የሰንበት ተማሪዎች ዛሬም ደግመን ጌታን እያመሰገንን በሀገራችን በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በመካሄድ ላይ ስላለው በጎ እድገት ጌታን እያመሰገንን በጎደለው ቅጥር የሚጠገን የሚፈውስ ጌታ እራሱ ለሀገራችን እንዲደርስልን ዛሬም በያለንበት እንድንተጋ በጸሎት ብርቱ ጥያቄያችንን እናቀርባለን፡፡ እኛም በያምና በጸሎት እንጋደላለን፡፡

በመጠነኛ ኑሮ የሚኖሩት የእንግሊዝኛው አሳታሚዎች ከጅማሬው እስከ ዛሬ ትርጉሙ እንዲዘጋጅ እንዲታተምና እንዲሰራጭ ለሚያደርጉት ትብብር እናመሰግናለን፡፡

የምጽአቱ የምሥራች የእንግሊዝኛ አገልግሎቱን በጸሎት ለሚደግፉት የአሜሪካ የጸሎት ሀብረት ወገኖችና በኢትዮጵያም ለሚገኙ የጸሎት አጋሮቻችን ምስጋናችን የላቀ ነው ዛሬም ጸሎታችሁን እንሻለን፤ በብርቱ ጸልዩልን፡፡ በእስራኤል ታሪክ በአሜሪካና በሌሎች ሀገሮችም የደረሰው የርስ በርስ እልቂትና ክፋት ዘረኝነት፣ ጥላቻ ከሀገራችን ኢትዮጵያ ሊወገድ የሚችለው በእግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ሀገራችን ኢትዮጵያን በጸሎታችሁ እንድታቀርቡ በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን (መዝሙረ ዳዊት 68፡31)፡፡

ማሳሰቢያ

የምጽአቱ የምስራች የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት በበጎ ፈቃድ የሚካሄድ አገልግሎት ነው፡፡ ለአገልግሎቱ የአንባቢያን ጸሎት የገንዘብ ድጋፍና የማበረታቻ መልእክቶችን በብርቱ እንፈልጋለን፡፡

የሚቻላችሁን ሁሉ በማድረግ የጌታን ሥራ እንድትተባበሩ በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን፡፡

- የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት ተርጓሚና፣ አስተባባሪ አደፍርስ/ኤዲ/ ሀብቴ መካሻ
- የኢትዮጵያ ተጠሪ አልማዝ አሳየ
- የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ
- ስልክ ቁጥር 0912120402